ትንቢተ ዕንባቆም(Habakkuk)

ምዕራፍ 1።

1፤ ነቢዩ ዕንባቆምያየ ውሽከምይህ ነው።

2፤ አቤቱ፥ እኔ ስጮኻየ ሟሰማውእስከ መቼ ነው? ስለ ግፍ ወደ አንተ እጮኻለሁ፥ አንተምአታድንም።

3፤ በደልንስ ስለ ምን አሳየኸኝ? ጠማማ ትንስ ስለ ምን ትመለከታለህ? ጥፋትና ግፍ በፊቴ ነው፤ ጠበና ክርክር ይነሣሉ።

4፤ ስለዚህ ሕግ ላልቶአል፥ ፍርድምድልነ ሥዶ አይወጣም፤ ኃጢኣተኛ ጻድቅን ይከብባልና፤ ስለዚህ ፍርድ ጠምጣሆኖ ይወጣል።

5፤ እናንተ የምትንቁ ሆይ፥ አንድ ቢተርከላችሁስንኳየ ሚዛምኑትን ሥራ በዘመናችሁእሠራለሁና እዩ፥ ተመልከቱ፥ ተደነቁ።

6፤ እነሆ፥ የእነርሱያልሆነ ወን መኖሪያ ይወርሱዘንድበምድር ስፋት ላይ የሚዳትን መራሮችንና ፈጣኖችን ሕዝብከለዳወያንን አስነሣለሁ።

7፤ እነርሱየሚያስፈሩና የሚያስደነግጡናቸው፤ ፍርዳቸውና ክብራቸውከራሳቸውይወጣል።

8፤ ፈረሶቻቸውምከነብር ይልቅ ፈጣኖች ናቸው፥ ከማታምተኩላ ይልቅ ጨካኞች ናቸው፤ ፈረሰኞቻቸውም ይንሳፈፋሉ፥ ከሩቅምይመጣሉ፥ ለመበልምእንደሚሹልንስር ይበርራሉ።

9፤ ሁሉምለግፍ ሥራ ይመጣሉ፥ ፊታቸውንምእንደ ምሥራቅ ነፋስ ያቀናሉ፤ ምርኮኞችንምእንደ አሸዋ ይሰበስባሉ።

10፤ በነገሥታት ላይ ያላግጣሉ፥ መሳፍንትምዋዛ ሆነ ወላቸዋል፤ በምሽጉ ሁሉ ይስቃሉ፥ አፈሩንምከምረው ይወስዱታል።

11፤ የዚያን ጊዜምእንደ ነፋስ አልፎ ይሄዳል፥ ይበድልሜል፤ ኃይሉንምአምላክ ያደርገዋል።

12፤ አቤቱ፥ የተቀደስህ አምላኬ ሆይ፥ አንተ ከዘላለምጀምሮ አልነበርህምን? እኛ አንሞትም፤ አቤቱ፥ ለፍርድ ሠርተኸዋል፥ ለተግሣጽምአድርገኸዋል።

13፤ ዓይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው፥ ጠማማ ትንምትመለከት ዘንድአትችልም፤ አታላዮችንስ ለምን ትመለከታለህ? ኃጢኣተኛወስ ከእርሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነ ወን ሲውጠውስለ ምን ዝምትላለህ?

14፤ ሰዎችንምእንደ ባሕር ዓሣዎች፥ አለቃምእንደሌላቸውተንቀሳቃሾች ለምን ታደርጋቸዋለህ?

15፤ ሁሉን በመንጠቆን ያወጣል፥ በመረቡምይይዛቸዋል፥ በአሽከላውምወስጥ ያከማቻቸዋል፤ ስለዚህ ደስ እያለውእልል ይላል።

16፤ እድል ፈንታውበእነ ርሱ ሰብታለችና፥ መበሉምበዝቶአልና ስለዚህ ለሚቡ ይሠዋል፥ ለአሽከላወም ያጥናል።

17፤ ስለዚህ ሚቡን ይጥላልን? አሕዛብንምዘወትር ይገ ድል ዘንድ አይራራምን?

ምዕ ራፍ 2።

1፤ በማስበቂያዬ ላይ እቆማለሁ፥ በአምጣ ላይምእወጣለሁ፤ የሚገ ረኝንም፥ ስለ ክርክሬምየ ምመልሰወን አወቅ ዘንድ እመለከታለሁ።

2፤ እግዚአብሔርምመለሰልኝ እንዲህምአለ። አንባቢውይፈጥን ዘንድ ራእዩን ጻፍ፥ በጽላትምላይ ግለጠው።

3፤ ራእዩ ገና እስከ ተወሰነ ውጊዜ ነው፥ ወደ ፍጻሜውምይቸኳል፥ እርሱምአይዋሽም፤ ቢዘገ ይምበእርግጥ ይመጣልና ታገ ሠው፤ እርሱ አይዘገ ይም።

4፤ እነ ሆ፥ ነ ፍሱ ከፍ ታለች፥ በወስጠምቅን አይደለችም፤ ጻድቅ ግን በእምነ ቱ በሕይወት ይኖራል።

5፤ እርሱ አታላይና ኩሩ ሰውነ ው፤ በስፍራውዐርፎ አይቀመጥም፤ ስስቱን እንደ ሲኦል ያሰፋል፥ እርሱምእንደ ሞት አይጠግብም፤ አሕዛብንምሁሉ ወደ እርሱ ይሰበስባል፥ ወገ ኖቹንምሁሉ ወደ እርሱ ያከማቻል።

6፤ እነ ዚህ ሁሉ። ለእርሱ ያልሆነ ወን ወደ እርሱ ለሚበስብ መያዣመንምለራሱ የሚበዛ ወዮለት! እስከ መቼ ነ ወ? እያሉ ምሳሌ አይመስሉበትምን?

7፤ ተረትምአይተርቱበትምን? የሚ ከሱህ ድንገ ት አይነ ሣብህምን? የሚያስጨነቁህምይነ ቃሉ፤ ለእነ ርሱም ብዝበዛ ትሆናለህ።

8፤ የሰወን ደምስላፈሰስህ፥ በምድሪቱና በከተሞቹምበእርስዋምበሚኖሩ ሁሉ ላይ ስላደረግኸውግፍ፥ አንተ ብዙዎችን አሕዛብን በዝብዘሃልና ከአሕዛብየ ቀሩት ሁሉ ይበዘብዙሃል።

9፤ ከክፉ እንዲድን ጐጆውን በከፍታላይ ያደርግ ዘንድ ለቤቱ ክፉ ትርፍን ለሚበስብ ወዮለት!

10፤ ብዙ አሕዛብን አጥፍተሃልና ለቤትህ እፍረትን ማከረሃል፥ በነ ፍስህምላይ ኃጢኣትን አድርገ ሃል።

11፤ ድንጋይምከግንብ ወስጥ ይጮኻል፥ እንጨትምከወቅር ወስጥ ይመልስለታል።

12፤ ከተማን በደምለሚሠራ፥ ከተማንምበኃጢኣት ለሚሞርት ወዮለት!

13፤ እነ ሆ፥ አሕዛብስለ እሳት እንዲሠሩ፥ ወገ ኖችምስለ ከንቱነ ት እንዲደክመከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድየ ሆነ አይደለምን?

14፤ ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለችና።

15፤ ኀፍረተ ሥጋወን ለማ ት ባልንጀራውን ለሚያጠጣ ከፉንምለሚጨምርበት፥ ለሚያሰከረውምወዮለት!

16፤ በከብር ፋንታ እፍረት ሞልቶብሃል፤ አንተ ደግሞ ጠጥተህ ተንገድገድ፤ የእግዚአብሔር የቀኙ ጽዋ ይመለስብሃል፥ እፍረትም በከብርህ ላይ ይሆናል።

17፤ የሰማንም ደምስላፈሰስህ፥ በምድሪቱና በከተሞቹም በእርስዋም በሚኖሩ ሁሉ ላይ ስላደረግኸው ግፍ፥ በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ ይከድንሃል፤ የአራዊትም አደጋ ያስፈራራሃል።

18፤ የተቀረጸ ማኽል ሠሪውየ ቀረጸው ለምን ጥቅም ነው? ዲዳን ምጣዖት ይሠራ ዘንድ ሠሪውየ ታመነ በቱ፥ ሐሰትን የሚያስተምር ቀልጦ የተሠራ ምን ይጠቅማል?

19፤ እንጨቱን። ንቃ፥ ዲዳውን ምድን ጋይ። ተነሣ ለሚል ውመዮለት! በውኑ ይህ ያስተምራልን? እነሆ፥ በወርቅና በብር ተለብጦአል፥ ምንም እስትንፋስ የለበትም።

20፤ እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል።

ምዕራፍ 3።

1፤ የነቢዩ የዕንባቆም ጸሎት በማዘሞ።

2፤ አቤቱ፥ ዝናህን ሰምቼ ፈራሁ፤ አቤቱ፥ በዓመታት መካከል ሥራህን ፈጽም፤ በዓመታት መካከል ትታወቅ፤ በመዓት ጊዜ ምሕረትን አስብ።

3፤ እግዚአብሔር ከቴማን፥ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል። ክብሩ ሰማያትን ከድኖአል፥ ምስጋናውም ምድርን ሞልቶአል።

4፤ ፀዳሉም እንደ ብርሃን ነው፤ ጨረር ከእጁ ወጥቶአል፤ ኃይሉም በዚያ ተሰወሮአል።

5፤ ቸነፈር በፊቱ ይሄዳል፥ የእሳትም ነበልባል ከእግሩ ይወጣል።

6፤ ቆመ፥ ምድርንም አወካት፤ ተመለከተ፥ አሕዛብንም አናወጠ፤ የዘላለምም ተራሮች ተቀጠቀጡ፥ የዘላለምም ኮረብቶች ቀለጡ፤ መንገዱ ከዘላለምነው።

7፤ የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ፤ የምድያምአገር መጋረጃዎች ተንቀጠቀጡ።

8፤ በውኑ እግዚአብሔር በወንዞች ላይ ተቈጥቶአልን? ቍጣህ በወንዞች ላይ፥ መዓትህም በባሕር ላይ ነውን? በፈረሶችህና በማዳንህ ሰረገሎች ላይ ተቀምጠሃልና።

9፤ በቃልህ እንደ ማልህ መቅሠፍትህን አወጣህ፤ ቀስትህንም ገተርህ፤ ምድርን ሰንጥቀህ ፈሳሾችን አወጣህ።

10፤ ተራሮች አንተን አይተውተጨነቁ፤ የውኃ ጎድአልፎአል፤ ቀላዩም ድምፁን ሰጥቶአል፥ እጁንም ወደ ላይ አንሥቶአል።

11፤ ፍላጾችህ ከወጡበት ብርሃን የተነሣ፥ ከሚያብለጨልጭ ጦርህ ፀዳል የተነሣ፥ ፀሐይና ጨረቃ በመኖሪያቸው ቆመ።

12፤ በምድር ላይ በመዓት ተራመድህ፤ አሕዛብን በቍጣ አሄደሃቸው።

13፤ ሕዝብህን ለማዳን፥ የቀባኸውን ለማዳን ወጣህ፤ የኃጢአተኛውን ቤት ራስ ቀጠቀጥህ፤ መሠረቱን እስከ አንገቱ ድረስ ገለጥህ።

14፤ የአለቆችን ራስ በገዛ በትራቸውጋህ፤ እኔን ይበትኑ ዘንድ እንደ ዐውሎነፋስ መጡ፤ ችግረኛውን በስውር ለመዋጥ ደስታቸውነ ው።

15፤ ፈረሶችህን በባሕር፥ በብዙ ውኆችምላይ አስረገጥህ።

16፤ እኔ ሰምቻለሁ፥ ልቤምደነገጠብኝ፤ ከድምፁየተነሣከንፈሮቼ ተንቀጠቀጡ፤ መንቀጥቀጥ ወደ አጥንቶቼ ወስጥገባ፤ በስፍራዬ ሆኜ ተናወጥሁ፤ በሚያስጨንቁን ሕዝብላይ እስኪመጣድረስ የመከራን ቀን ዝምብዬ እጠብቃለሁ።

17፤ ምንምእንኳበለስምባታፈራ፥ በወይንምሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችምመበልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችምበጋጡወስጥ ባይገኙ፥

18፤ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ።

19፤ ጌታእግዚአብሔር ኃይሌነ ው፤ እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችምላይ ያስሄደኛል።